**በደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቤዛ-ኲሉ ሰንበት ትምህርት ቤት የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለአምላካችን ፣ ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የቀረበ ሥነ-ግጥም።**

«እግዚአብሔር አብ በሰማይ ሆኖ ምሥራቅንና ምዕራብን፣ ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችን ሁሉ በእውነት ተመለከተ። ተነፈሰ አሻተተም፤ እንደ አንቺ ያለ አላገኘም፤ የአንቺን መዓዛ ወደደ፤ ደም ግባትሽንም ወደደ፤ የሚወደውን ልጁንም ወዳንቺ ሰደደ።»

*አባ ሕርያቆስ፥ቅዳሴ ማርያም*

# ቃልና ማደሪያው

በሰሜን በደቡብ ቃኘት አረገና፣
በምሥራቅ በምዕራብ ተመለከተና፣
ከሰማይ ወደ ምድር በዓይኑ አማተረና፣
ከፈጠረው ፍጥረት አንዲት አገኘና፣
ለቃሉ ማደሪያ ንጹሕ መረጠና፣
መልአኩን ላከባት ልቧን አወቀና።

ቃል ቦታውን ያዘ ትንቢት አከበረ፣
የድንግል ማሕፀን ልዑል አሳደረ።
ሰይጣን ተስፋ ቈረጥ ትንቢቱ ደረሰ፣
የድንግል ማሕፀን አዳኙን ጸነሰ።
የተፈጥሮን ክስተት ሕጉን ሻረውና፣
ማሕፀኗን ባርኮ ሽላለመውና፣
ጥቂት ከሥጋዋ ሥጋን ወሰደና፣
ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ተዋሐዳትና፣
እንደ ሰው በሆዷ ሂደቱን ጨርሶ፣
ምድር ዋለ ኢየሱስ ሊያድን ሥጋ ቆርሶ።

የሰማዩ ንጉሥ በምድርም ነገሠ ፤
አዳምን ለማዳን ቃል ሥጋ ለበሰ።
ሰው አምላክ ለመሆን ሞክሮ ተሳነው፤
አምላክ ግን ሰው ሆኖ ፍጥረትን አዳነው።

ሞትህ እንቅልፍ ሆኗል አዳም በቃህ ተነሥ፣
አዳኝህ ተወልዷል በምድር ሊመላለስ።
ለሞት ያበቃችህ የትናንትዋ ፍሬ፣
በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልዋ ደክሟል ዛሬ።
ኢሳይያስ በትንቢት የመሰከረለት፣
ነቢዩ ሕዝቅኤል ራእይ ያየለት፣
ቃል ሥጋ መልበሱ የተነገረለት፣
ተወለደ አማኑኤል ይኸው በዚች ዕለት።
ዓለም ሳይፈጠር ከጥንት የነበረ፣
በመንፈስ በስሙ በአብ የከበረ፣
ሞትን ድል ሊነሳ ከመቃብር ወርዶ፣
በረት ተወለደ ራሱን አዋርዶ።

የዕድሜ ልክ ደስታ በተአምራቱ ቀን፣
ሕያው ተወለደ ከድንግል ማሕፀን።
ምድርን በውኃ ላይ ያንጠለጠለውን፣
ሰማይን ያለ አጋር ችሎ ያጸናውን፣
በፀሐይ ብርሃን ቀን ያደመቀውን፥
ሌቱን በጨረቃ ያሸበረቀውን፣
አዳምን በእስትንፋስ በአፈር ያበጀውን፣
ዓለምን ያስዋበ ያሰማመረውን፣
ያልነበረን ማኖር መፍጠር ያልተሳነው፣
የማይወሰነው ተወስኖ አየነው።

የሰው ልጅ ኅሊና የማይመረምረው፣
የድንግል ማሕፀን ዘጠኝ ወር አኖረው።
ሰማይና ምድርን በክብሩ ያዘዘው፣
ክርስቶስ ሲወለድ አንድ ግርግም ያዘው።
የፍጥረት ባለቤት የሕይወት መገኛው፣
አንድ ጉያ አቀፈ ኲርማን ቦታ አስተኛው።
ሰውን በቃል ፈጥሮ በቃል ያሳደረ፣
በከብቶች መኖሪያ በበረት አደረ።
መና ከሰማይ ላይ ለምድር ያዘነበው፣
ጌታ ክርስቶስን የእናት ጡት መገበው።

ቃሉ የፈጠረ እጁ ያበጃቸው፣
በዓለም ላይ አስውቦ ያሰማመራቸው፣
እንደ ሰውም ባይሆን እንስሳት በዐቅማቸው፣
ለእጅ መንሻ የሚሆን ከርቤ ባይኖራቸው፣
ወርቅና ዕጣን ይዞ ባይደርስ አካላቸው፣
የዐቅሙን አበርክቷል ሙቁ ትንፋሻቸው።

ሰብአ ሰገል ታዘው በኮከብ ተመርተው፣
ሕፃኑን ካለበት ከግርግም አግኝተው፣
በረከት የሚሆን ያላቸውን ሰጥተው፣
ስለ ቃሉ አደሩ ሄሮድስን ረስተው።
የንጉሦች ንጉሥ በተወለደበት ፣
ስሙ ከአጥናፍ አጥናፍ በተነገረበት፣
ዕልልታ ምስጋና ሆታና ዝማሬ፣
ለኢየሱስ ክርስቶስ ይገባዋል ዛሬ።

በድቅድቅ ጨለማ ፍጥረት ሲመላለስ፣
«ሀ» ሲባል ተዋርዶ ተረግሞ በበለስ፣
አንገትህን ያስደፋህ ኃጢአት ያሳፈረህ፣
የአዳም ዘር ቀና በል ዛሬማ ተምረህ፣
ምን ማኅንበስ አለ ቀና በል አትፍራ፣
ሕፃኑ ወሰደው የሞትህን መከራ።
ጌታ መወለዱን ፍጥረት መሰከረ፣
ኮከቧ ጠቆመች የት ውሎ እንዳደረ።

## በደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ትምህርት ቤት የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ለአምላካችን ፣ ለጌታችንና ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል የቀረበ ሥነ-ግጥም።

ፈሳሹ በወተት በማር ተለወጠ፣
ተራራው ዘለስ ምድር ተናወጠ።
የበረከት ፍሬ ከእንጨቶች ተገኘ፣
የምሥራቹ ቃል ከአጥናፍ አጥናፍ ናኘ።
ምድርና መላዋ ጌትነቱን አውቀው፣
የመልኩ አምሳያዎች ሰገዱለት ወድቀው።
የነቢያት ትንቢት ቃላቸው ታተመ፣
«አዳኝ ይወለዳል» ያሉት ተፈጸመ።

ሄሮድስ አስጠራቸው ሊቀ ሊቃውንቱን፣
መወለዱን ሰምቶ ክርስቶስ መምጣቱን።
አዋጅ ወጣ በአገር ከተማው ታመሰ፣
የስንቱ ጨቅላ ደም በራማ ፈሰሰ።
ገና ሳይጠነክር እንደ ተወለደ፣
በምድረ በዳው ላይ ሕፃን ተሰደደ።
በፈጠረው ምድር ተመላለሰበት፣
በእሾህ በለምለሙ ተስተናገደበት።
ቢገኝ ይፈውሳል እግሩ ያረፈበት፣
ዘርፋፋ ቀሚሱ መሬት ያሰሰበት።
መድኃኒት ይሆናል ላመነው በክብር፣
ይኼ ኃያል ንጉሥ የረገጠው ምድር።

ከሞት ዕዳ አውጥቶ ከኃጢአት ላዳነን፣
ልባችንን መሰበር እንደምን ተሳነን።
የሥላሴን ምሥጢር ጥበቡን ነገረን፣
ወልድ ወረደ ምድር በቃሉ አስተማረን።
የጽላቱን ላይ ቃል አምላክ የቀረጸው፣
ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ በውል የገለጸው፣
ሰው አልሆነለትም ድክመቱ ታገለው፣
ስሙ ይክበርልን ክርስቶስ ፈጸመው።

እንግዲህ የሰው ልጅ ማዳኑን ተረድተህ፣
ስለ ጌታህ እደር ሁሉንም እረስተህ።
እንደ ትውልዱ ቀን ልደቱ ሲከበር፣
ተአምር እንዳትጠብቅ ለየት ያለ ነገር።
የልደት ስጦታ ከርቤ አልተጠየቀም፣
ዛሬ ለእጅ መንሻ ወርቅ አልተፈለገም፣
አሁን ተፈላጊው ካንተ እሚጠበቀው፣
ልብን አዘጋጅቶ ለአምላክህ ማቅረብ ነው።

ፍቅር አይራቅ ካንተ ተስማማ ከሁሉ፣
እንዳለው ተራመድ እደር እንደ ቃሉ።
መንገዱ ከቀና ውስጥህ ካማረበት፣
የበረከት እንጨት ፍሬው ከፈራበት፣
ደጃፍ እያንኳኳ አስገባኝ የሚልህ፣
ከነበረከቱ ቆሟል ከበራፍህ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍርድህ ትክክል ነው፣
ለሕዝብህ ደግነት ማስተዋልን ስጠው።
ይበላለጥ እንጂ የሰው የምድር ሥራ፣
በአንተ ዓይን እኩል ነው ንጉሥና ተራ።
ስትሰጥ ስስት አታውቅ ሥጋና ደም ለጋስ፣
ላንተ እንግዳ አይደለም ተበድለህ መካስ።
ምሕረት ቸርነትህ ትዕግሥትህ ይብዛልን፣
ላጠፋነው ጥፋት ቁጣህ ይራቅልን።
አንተ በቃችሁ በል የዚህ ዓለም ዳኛ፣
ዓርባ ቀን ዓርባ ዓመት ሆኖብናል ለእኛ።
አውቀን በድለናል ይቅርታ አድርግልን፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያን ጎብኝልን።

ታርዛለችና ክብርህን አልብሳት፣
ተርባለችና ቃልህን መግባት፣
ተጠምታለችና ጥበብህን አጠጣት፣
አቤቱ ጌታችን ዳብሳት በጆችህ ጣት።
ለሰው የማይቻል ይቻልሃልና፣
ሰላም ፍቅርን ስጣት ቸር አምላክ ነህና።

ተለማኝ አምላክ ነህ ስለማርያም ስትል፣
ሁሉ ይቻልሃል እርዳን እናስተውል።
የበረከት አምላክ ትባርከናለህ፣
ኤልሻዳዩ ጌታ እግዚአብሔር ታላቅ ነህ።

ታኅሣሥ ፳፱ /፲፱፻፹፱
ካይሮ
አብርሃም ሰሎሞን።

ያቺን ቀን በጸፍጸፍ
ከሚለው መጽሐፍ ላይ የተወሰደ።